**የአፍሪካ ሰብዓዊ ድርጅት የወደፊት ትኩረት**
**የ25ኛ ዓመት አከባበር**

**መሰናዶ**

ስደተኞችንና ተፈናቃዮችን መልሶ ማቋቋምን አልሞ የተመሰረተው አፍሪካ ሰብዓዊ ድርጅት የ25ኛውን የልደት በዓል አክቶበር **23-25 2019** በኪጋሊ ከተማ (ሩዋንዳ) ለማክበር በዝግጅት ላይ መሆኑን ሲያበስር ኩራት ይሰማዋል፡፡

አክቶበር **23/2019** ደርጅቱ የ**25** ዓመቱን ጥረት የሚቃኝበት፣ያለፈውን ትርጉም ያለው እንቅስቃሴውን የሚያስቀጥልበት፣ የወደፊት አካሄዱን የሚጠቁም ፍኖተካርታ ይፋ የሚያደርግበት ይሆናል፡፡

በተጨማሪም አክቶበር **24** እና **25 2019** የአፍሪካ ህብረት ለወጠነው "የስደተኞች ተመላሾችና ተፈናቃዮች ዓመት፡- በአፍሪካ የመፈናቀል ችግር ዘላቂ መፍትሄ" የሚለውን የዓመቱን ርዕስ ከአፍሪካ ህብረትና ከተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የስደተኛ ኮሚሽነር UNHCR ጋር ሆነን በጥረት አንድነትና ሃላፊነትን በጋራ በመወጣት ላይ ያተኮረ በአህጉራዊ ምክክር ጉባዔ (አ.ም.ጉ) መልክ የምንሰበሰብበት ይሆናል፡፡

ኤ ኤች ኤ በሳል ልምድ ባላቸው ኢትዮ□ያውያን ባለሙያዎች በ**1994**ተቋቋመ፡፡ በወቅቱ ጎልቶ የተከሰተውን የሩዋንዳ ችግር በመዳሰስ ከሰባት አፍሪካ ሀገሮች የተውጣጡ **13**በጎ ፈቃደኞች ጋር ሆኖ ችግሩን እንዲመለከት ተወሰነ፡፡ ከዚህ ወቅት ጀምሮ ባደረገው ፈጣንና የተሟላ እንቅስቃሴ አፍሪካ ሰብአዊ ድርጅት ከ**25** ሚልየን ሰዎች በላይ በ**20** አፍሪካ ሀገሮች ለመርዳት ተችሏል፡፡ እንቅስቃሴ የተካሄደባቸው ሀገሮች ኦፐሬሽናል ካንትሪስ አልጀሪያ፣ አንጎላ፣ ቡሩንዲ፣ ካሜሩን፣ ቻድ፣ ጂቡቲ፣ ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ኢትዮ□ያ፣ጊኒ (አንካራ)፣ኬኒያ፣ላይቤሪያ፣ናሚቢያ፣ ሴራሊዮን፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ እና ዛምቢያን ያካትታል፡፡

ዋና መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገው ኤ ኤች ኤ ለስደተኞችና ለተፈናቃዮች እርዳታና ተስፋ እንዲሆን የወደፊት ተስፋቸውም እንዳይጨልም ሲል ፤ በጤናና በጽዳት፤በምግብ ዋስትናና በአመጋገብ ስርዓት፤ በትምህርት፤በመጠለያና መሰረተ ልማት፤ በቅንጅትና በሎጂስቲክስ፤ በእንክብካቤና ዘላቂ ኑሮን በማረጋገጥ መስኮች በጠቅላላ **190** ሚልየን ዶላር ወጪ አድርጓል፡፡

ኤ ኤች ኤ ከሀገር ውስጥ ማህበራትና ከአለም አቀፍ ተባባሪዎች አብሮ በመስራት ሰብአዊ እርዳታ ያበረክታል፡፡ የሀገር ውስጥ ማህበራትን ያበረታታል፤ የተፈናቃዮችን አደጋ የመቋቋም ሀይልና ማህበራዊ መሰረት ያላቸው የረጅም ጊዜ የልማት ፕሮጀክቶችን ያጠናክራል፡፡

አፍሪካውያን በማህበረሰብ ተኮር ስልጣን እንዲላበሱ ከመሻትና ከመጣር አኳያ፤ ኤ ኤች ኤ በአቅም ግንባታ፤ አደጋ ባወደማቸው ስፍራዎች የጤና እንክብካቤ ጣቢያዎችን በማቋቋም አዲስ ሆስፒታሎችንና የጤና ማዕከሎችን በመስራት፤ ውሃ ጉድጓድና ትምህርት ቤቶች በመገንባት የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በማሰልጠን መስኮች ጉልህ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው፡፡

በቅልጥፍናው፤ ተጠያቂነቱን በመወጣትና በግልፅነቱ ዝና በማትረፍ ላይ ያለው ኤ ኤች ኤ ለእርዳታ ድርጅቶችና የደጋፊዎች ተኣማኒነቱ ከማረጋገጥ ባሻገር የዓለም አቀፍ ሂሳብ መርማሪ ድርጅቶች አዎንታም አግኝቷል፡፡

ግንባር ቀደም ተግባሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ኤ ኤች ኤ በሚጫወተው አለም አቀፍ ሚና አማካኝነት፤ በሰሜን ሀገሮች ሙሉ በሙሉ ተይዞ በነበረው መድረክ ላይ የአፍሪካ ድምፅ መሰማት እንዲጀምር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ያሁኑ የአፍሪካ ቁመና በጎ ለውጥ የሚያስተናግድ እንጂ የማያቋርጥ ቀውስ አስተናጋጅ አህጉር አለመሆኑን ማስረገጥ የረጅም ጊዜ ኤ ኤች ኤ ግብ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን እጅግ ድንቅ የሆነውን የአፍሪካ ሰብአዊነት ተምሳሌት መሆናችንን ልናሰምርበት እንወዳለን፡፡

**የሚዲያ ግንኙነት፡ ማህሌት ዘር□ያእቆብ**
communications@africahumanitarian.org, +251(0)11660-4800/660-3700
www.africahumanitarian.org